# ለአንበሳ ኢንተርናሽል ባንክ (አ.ማ.) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች ጥቆማ ለመቀበል የወጣ ማስታወቂያ

የአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ.) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቋማዊ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ኤስ.ቢ.ቢ./71/2019 መሠረት በ17ኛ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የቦርድ አባላት የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ አባላትን መርጧል፡፡

በዚህም መሰረት የምልመላና ምርጫ ኮሚቴው ከባለአክስዮኖች የሚቀርብለትን የቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ ለመቀበል የሚያስችለው ዝግጅት ያጠናቀቀ ስለሆነ፤ ለቦርድ አባልነት መስፈርት የሚያሟሉ ዕጩዎችን ከግንቦት 01 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከባለአክስዮኖች ጥቆማ የሚቀበል መሆኑን በአክብሮት ያሳውቃል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤስ.ቢ.ቢ./71/2019 እና ኤስ.ቢ.ቢ./79/2021 መሠረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባልነት የሚጠቆሙ ዕጩ አባላት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. በባንኩ ባለአክስዮን የሆነ/ች፣
2. ዕድሜ 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ/ች፣
3. በማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ/ች፣
4. የምልምላ እና ምርጫ ኮሚቴ አባል ያልሆነ/ች፣
5. ሀቀኛ፣ ታማኝ እና መልካም ዝና ያለው/ያላት፣
6. ቦርዱ በቂ የፆታ፣ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ስብጥር ያለው እንዲሆን ለማስቻል ተጠቋሚ ዕጩው/ዋ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ኖሮት/ኖሯት በባንክ፣ በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በማናጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በንግድ ሥራ አስተዳደር፣ በኦዲት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እና በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት የሙያና የሥራ ዘርፎች ልምድ ያለው/ያላት ቢሆን ይመረጣል፣
7. በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የቦርድ አባል ያልሆነ/ች፣
8. በማጭበርበር፣ ዕምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት/ተሰጥቶባት የማያውቅ/የማታውቅ፣
9. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ያልቀረበባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ያልተሰጠባት፣
10. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሐራጅ ጨረታ ያልተሸጠበት/ያልተሸጠባት፣ ተከሶ ያልተፈረደበት/ያልተፈረደባት ወይም እሱ የሚመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት/የሆነችበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ ብድር ያልዞረበት/ያልዞረባት ወይም ያልገባበት/ያልገባባት፣

11. በቂ ስንቅ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በመስጠቱ ሂሳቡ ያልተዘጋበት/ያልተዘጋባት፣
12. ግብር ባለመክፈል ተከስሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያልተባለ/ች፣
13. የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በዕጩነት ሊጠቆም ይችላል፣
14. ከሚጠቆሙት 22 ዕጩዎች መካከል 1/3ኛ (ስምንቱ) የሚጠቆሙት ከባንኩ ጠቅላላ አክስዮን ከ2% በታች አክሲዮን የያዙ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች (Non-Influential Shareholders) ብቻ ሲሆን፣ ተጠቋሚው/ዋ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ/ች ባለአክስዮኖች ብቻ መሆን አለበት/ባት፡፡
15. ቀሪዎቹ 2/3ኛ (አስራ አራቱ) ዕጩዎች ሁሉም ባለአክስዮኖች በጋራ ከሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚጠቆሙ ናቸው፡፡
16. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተገለጹ ሌሎች መመዘኛዎችን የሚያሟላ/ምታሟላ፡፡

**ስለሆነም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክስዮኖች ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጪዎችን በሚከተሉት የጥቆማ መቀበያ መንገዶች በመጠቀም በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቆማችሁን ለምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴው እንድታቀርቡ ተጋብዛችኋል፡፡**

## ➢ የጥቆማ መቀበያ መንገዶች፣

1. 22 ሌክስ ፕላዛ ሕንጻ በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 705 በሚገኘው የምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ጊዜአዊ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ በተዘጋጀው ቅፅ በመሙላት፣
2. ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ እና ፈርሞ በፋክስ ቁጥር +251-116181188 ወይም ተሞልቶ የተፈረመውን ቅፅ ስካን ኮፒ (scan-copy) በማድረግ በኢሜይል አድራሻ nomination-committee@anbesabank.com በመላክ፣
3. በፖስታ ሳጥን ቁጥር 27026/1000 በመላክ፣ ወይም
4. ለዚሁ ተግባር በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች የተቀመጡ ቅፆችን ሞልቶ እና ፈርሞ ለቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ወይም ለሚወክለው ሰው በማስረከብ ጥቆማ መስጠት ይቻላል፡፡
5. በተጨማሪም ለባለአክስዮኖች መጠቆሚያ የተዘጋጀው ቅፅ ከባንኩ ዌብሳይት https://www.anbesabank.com/ ማውረድ ወይም ከምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ጽ/ቤት በመውሰድ እና ቅፁን ሞልቶ በመፈረም መመለስ ይቻላል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች +251-16672510 ወይም +251-16626000/60-መደወል ይቻላል፡፡**

**የአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ**